የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፩
አዲስ አበባ መስከረም ፲፫ ቀን ፲፱፻፺፪

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

6th Year No. 1
ADDIS ABABA - 24th Sept. 1999

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፶፯/፲፱፻፺፩ ዓ.ም.
የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች የሥነ ምግባር
ደንብ ........................................ ገጽ ፩ሺ፩፻፶፮

## CONTENTS

Council of Ministers Regulations No. 57/1999
Federal Court Advocates' Code of Conduct
Regulations ............................................ Page 1156

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፶፯/፲፱፻፺፩
### የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች የሥነ ምግባር ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች የሥነ ምግባር ደንብ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፶፯/፲፱፻፺፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ ደንብ የፌዴራል ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ በተሰጠው በማንኛውም ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

፫· አጠቃላይ መርህ

ማንኛውም ጠበቃ ሕግን ለማስከበርና ፍትሕን ለማስገኘት የፍትሕ አስተዳደሩን የማገዝ ኃላፊነት አለበት። ማንኛውም ጠበቃ በተለይም ለደንበኛው፣ ለሌሎች የሕግ ሙያተኞችና ተከራካሪ ወገኖች፣ ለፍርድ ቤት፣ ለሙያው እና በአጠቃላይ ለህብረተሰቡ ያለበትን የሙያ ኃላፊነት በቅንነት፣ በታማኝነት እና በእውነተኛነት መወጣት አለበት።

፬· ደንበኛን ስለመቀበል

ማንኛውም ጠበቃ የሕግ አገልግሎት ለማግኘት የመጣ ደንበኛን ጉዳይ ተቀብሎ የጉዳዩን ፍሬ ነገርና ማስረጃዎች ከመረመረ በኋላ ክርክሩ ሕጋዊ መሠረት የሌለው ከሆነ ጉዳዩን መያዝ የለበትም። ሆኖም ለሰጠው የሕግ ምክር አገልግሎት ተገቢውን ክፍያ ተቀብሎ ደንበኛውን ያሰናብታል።

ያንዱ ዋጋ 4.85
Unit Price

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS NO.57/1999
### COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO PROVIDE FOR THE FEDERAL COURT ADVOCATES' CODE OF CONDUCT

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definitions of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995.

1. *Short Title*

   These Regulations may be cited as the "Federal Court Advocates' Code of Conduct Council of Ministers Regulations No. 57/1999."

2. *Scope of Application*

   These Regulations shall apply to any person who is issued with a federal courts' advocacy license.

3. *General Principle*

   Any advocate shall have the responsibility to assist the organs of the administration of justice in the effort to promote respect for the law and the attainment of justice. Any advocate shall, in particular discharge his professional duty to his client, other lawyers and opposing party, the court, his profession, and the society in general honestly, faithfully and truthfully.

4. *Receiving Clients*

   Any advocate may not handle a case of a client seeking legal service where, after evaluating the facts and the evidence, the claim has no legal ground. However, he may collect reasonable fee for the legal advice he had rendered, and dismiss the client.

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፭· <u>አገልግሎት ለመስጠት ፈቃደኛ ስላለመሆን</u>

ማንኛውም ጠበቃ በአገልግሎት ጠያቂ ደንበኛው የሞራል ባህሪ፣ በተፈፀመው ወንጀል ከባድነትና አስነዋሪነት ወይም በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ ነው በሚል እምነት ወይም የደንበኛውን የፖለቲካ ፣ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ ወይም የሞራል አቋሙን መሠረት በማድረግ የጥብቅና አገልግሎት አልሰጥም ማለት አይችልም።

፮· <u>ከደንበኛ ጋር ስለሚደረግ ውል</u>

፩· ማንኛውም ጠበቃ ከደንበኛው ጋር በጽሑፍ የሰፈረ ግልጽ የውል ስምምነት ሊፈጽም ይገባል። ውሉም የተዋዋዮችን ስም፣ አድራሻ፣ የአገልግሎቱን ዓይነት፣ የውክልና ዓይነትና መጠን፣ የአገልግሎት ክፍያውን መጠን፣ ክፍያው የሚወሰንበትን ሥልትና የአከፋፈሉን ሥርዓትና የመክፍያውን ጊዜ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን የያዘ ይሆናል።

፪· አንድ ጠበቃ ለደንበኛው የገባውን የሙያ አገልግሎት በአግባቡ ባለማበርከቱ ምክንያት የሚኖርበትን የፍትሐ ብሔር ኃላፊነት የሚቀንስ ወይም የሚያስቀር ስምምነት ዋጋ የለውም።

፯· <u>የአገልግሎት ዓይነትና የውክልና መጠን</u>

፩· ማንኛውም ጠበቃ የደንበኛውን ጉዳይ ፍሬ ነገርና ማስረጃዎች ከመረመረ በኋላ በሕግ መሠረት በጉዳዩ ሊገኝ የሚችለውን ውጤት ወይም አማራጭ ውጤቶች እንዲሁም ተፈላጊውን ውጤት ለማግኘት ደንበኛው ለጠበቃው ሊሰጠው የሚገባውን የውክልና ዓይነትና መጠን በማስረዳት ከተገቢው ውሳኔ ላይ እንዲደርስ የመርዳት ግዴታ አለበት።

፪· ደንበኛው ከጠበቃው በተሰጠው የሕግ ምክር ላይ ተመስርቶ የሚሰጠው ውሳኔ ሕግንና ይህን ደንብ የማይጥስ እስከሆነ ድረስ ጠበቃው የማክበር ግዴታ አለበት። በተለይም ጉዳዩ በግልግል እንዲያልቅ ደንበኛው ከወሰነ ጠበቃው ውሳኔውን ማክበር አለበት።

፫· ደንበኛው የሚፈልገው የዕርዳታ ወይም የአገልግሎት ጥያቄ ይህን የሥነ ምግባር ደንብ ወይም ሌላ ሕግ የሚጥስ ከሆነ ጠበቃው አገልግሎቱን ሊሰጥ የማይችልበትን ምክንያት ለደንበኛው ማስረዳትና ደንበኛው ምክሩን ተቀብሎ የማያስተካክል ከሆነ ማሰናበት አለበት።

፬· ደንበኛው በውክልናው ላይ ውሳኔ ለመስጠት በመፈለግ መረጃ በጠየቀ ጊዜ ጠበቃው ተገቢውን ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችሉትን መረጃዎች በማቅረብ ውሳኔ ላይ እንዲደርስ መርዳት አለበት።

፰· <u>ብቃት ያለው አገልግሎት ስለመስጠት</u>

፩· ማንኛውም ጠበቃ በሚሰጠው የጥብቅና አገልግሎት ከፍተኛ የሙያ ችሎታና ብቃት ማሳየት ይጠበቅበታል።

፪· ጠበቃው ሕግ በሚፈቅደው መሠረት፣

ሀ) የደንበኛውን መብትና ጥቅም ለማስከበር ዕውቀቱና የሥራ ልምዱን በሥራ ላይ የማዋል፣

ለ) የደንበኛውን ጉዳይ በትጋት የመከታተልና አፋጣኝና ፍትሐዊ ውሣኔ ለማግኘት ሊወሰድ የሚገባውን እርምጃ ሁሉ በጥንቃቄና በወቅቱ የመፈጸም ሙያዊ ግዴታ አለበት።

፱· <u>አስፈላጊውን መረጃ ስለመስጠት</u>

ማንኛውም ጠበቃ ጉዳዩ የደረሰበትን ደረጃና የሚገኝበትን ሁኔታ በየጊዜው ለደንበኛው የማሳወቅ ግዴታ አለበት። ደንበኛው መረጃ እንዲሰጠው በጠየቀ ጊዜም አፋጣኝ ምላሽ የማግኘት መብት አለው።

5. *Declining Advocacy Service*

Any advocate may not decline to render advocacy service on grounds of the moral character of the client, the serious and heinous nature of the crime committed or the belief that the client is guilty of the crime charged, or on the basis of the client's political, economic, social or moral standings.

6. *Contract with Client*

1) Any advocate shall make a clear and written contractual agreement with his client. The contract shall include the names of the parties, address, type of service, type and scope of representation, the amount of fee, way of computation, mode and time of payment of the fee, and such other information as necessary.

2) An agreement restricting or totally avoiding the civil liability of the advocate due to the advocate's failure to render proper service to his client shall be of no effect.

7. *Type of Service and Scope of Representation*

1) An Advocate shall have the obligation, after evaluating the facts and evidences of the case, to assist his client reach on the proper decision by giving him explanation based on the law as to the possible result or alternative results of the matter, and the type and scope of representation that must be assumed to obtain the desired result.

2) The advocate shall respect the decision of the client made on the basis of the advice given by the advocate as long as the decision does not violate the law and these regulations. He shall, in particular, respect the decision made by the client to solve the matter by settlement.

3) When the assistance required or service requested by the client is in violation of these regulations or other law, the advocate shall explain the reason why he can not render service and dismiss the client if the client fails to make corrections based on the advice given.

4) The advocate shall provide the client with the relevant information and assist him reach at the appropriate decision when the client requests information seeking to give decision on the representation.

8. *Rendering Competent Service*

1) Any advocate is expected to show a high level of professional competence and skill in the advocacy service he renders.

2) An advocate shall have professional obligation, within the limits of the law:

(a) to employ his legal knowledge and work experience to protect the rights and interests of his client;

(b) to follow up his client's case diligently and take all the necessary measures carefully and timely so as to obtain a quick and just decision.

9. *Communication*

Any advocate shall have the obligation to keep informed his client with the stage the case has reached and its status. The client has the right to get a quick response when he requests for information.

፲· ምስጢር ስለመጠበቅ

፩· ማንኛውም ጠበቃ የደንበኛውን ግላዊ ወይም ድርጅታዊ መረጃ ወይም በሙያ አገልግሎቱ ምክንያት በእጁ የገባውን ማንኛውንም ሌላ መረጃ በምስጢር የመጠበቅ ሙያዊ ግዴታ አለበት።

፪· ጠበቃው በውክልናው ምክንያት ከደንበኛው የተሰጠውን መረጃ እና ማንኛውንም ሌላ መረጃ ከደንበኛው ፈቃድ ሳያገኝ ሊገልጽ አይችልም።

፫· የጠበቃ ምስጢር የመጠበቅ ሙያዊ ግዴታ በእርሱና በደንበኛው መካከል የነበረው የሥራ ውል በመቋረጡ ምክንያት ቀሪ ሊሆን አይችልም።

፲፩· ምስጢር ስለሚገለጽበት ሁኔታ

የአንቀጽ ፲ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ጠበቃው ተገቢ ነው ብሎ ሲያምን በሙያ ሥራው አጋጣሚ በእጁ የገባውን መረጃ በሚከተሉት ምክንያቶች እንደአስፈላጊነቱ መጠን ሊገልጽ ይችላል፡

፩· ከደንበኛው ያገኘው መረጃ ለተወከለበት ሥራ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ፣

፪· ከደንበኛው ጋር ክርክር በሚፈጠርበት ጊዜ ራሱን ለመከላከል ወይም መብቱን ለማስከበር፣

፫· የውክልና ሥልጣኑን የተመለከተ ክርክር ሲነሳ፣ ወይም

፬· ሕግ በሌላ ሁኔታ በግልጽ የጣለበትን ግዴታ ለመወጣት።

፲፪· የጥቅም ግጭት

ማንኛውም ጠበቃ በራሱና በደንበኛው ወይም በዘመዶቹና በደንበኛው ወይም በሽሪኮቹና በደንበኛው ወይም በሁለት ደንበኞቹ መካከል የጥቅም ግጭት መኖሩን እያወቀ የሙያ አገልግሎት ለመስጠት መዋዋል አይችልም። የጥቅም ግጭት መኖሩ የታወቀው አገልግሎቱ ከተጀመረ በኋላ ከሆነ ይሄንኑ ለደንበኛው አስረድቶ አገልግሎቱን ማቋረጥ አለበት።

፲፫· ከቀድሞ ደንበኛ ጋር ስለሚኖር የጥቅም ግጭት

፩· ማንኛውም ጠበቃ ከዚህ ቀደም የጥብቅና አገልግሎት ከሰጠበት ጉዳይ ወይም ከደንበኛው ጥቅም ጋር በሚጻረሩ ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት ባላቸው ሌሎች ጉዳዮች ላይ ከቀድሞ ደንበኛው ጋር ተመካክሮ የጽሑፍ ፈቃድ ካላገኘ በስተቀር ለአዲስ ደንበኛ የጥብቅና አገልግሎት ሊሰጥ አይችልም።

፪· ማንኛውም ጠበቃ ከዚህ ቀደም ይሰራበት የነበረው የጥብቅና አገልግሎት ድርጅት የጥብቅና አገልግሎት ከሰጠው ደንበኛ ጥቅም ጋር የሚጻረር ጥቅም ላለውና ስለደንበኛውም መረጃ ባገኘበት ጉዳይ ከቀድሞ የድርጅቱ ደንበኛ ጋር ተመካክሮ የጽሑፍ ፈቃድ ካላገኘ በስተቀር ለአዲሱ ደንበኛው የጥብቅና አገልግሎት ሊሰጥ አይችልም።

፲፬· በጠበቃና በደንበኛ መካከል የሚፈጸሙ ውሎች

ማንኛውም ጠበቃ ከደንበኛው ጋር ማናቸውንም ውል ሊዋዋል የሚችለው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ከተሟሉ ብቻ ነው፡

፩· በጠበቃውና በደንበኛው መካከል የሚደረገው ውል ከወቅቱና ከሁኔታዎች አንፃር ተገቢና ምክንያታዊ ሲሆን፣

፪· ጠበቃው የስምምነቶቹን መስፈርቶችና የውሉን ዓይነት ለደንበኛው በግልጽ ያስረዳው ከሆነ ፣ ወይም

፫· ደንበኛው በውሉ ላይ ከሌላ ሰው ጋር ተመካክሮ ስምምነቱን በጽሑፍ ያፀደቀ ሲሆን።

10. *Confidentiality of Information*

1) Any advocate shall have professional obligation to keep in secret the personal or organizational information of his client or any other information he obtained in the course of his professional service.
2) The advocate may not, without the consent of the client, reveal information relating to his power of representation and any other information.
3) The obligation of professional confidentiality of an advocate may not cease because of termination of the contract with the client.

11. *Condition of Disclosure*

Without prejudice to the provisions of Article 10, an advocate may, when he reasonably believes appropriate, reveal to the extent necessary the information he obtained in the course of his professional duties, in the following cases:

1) when the information he obtained from the client is necessary for the task he is represented;
2) to defend himself or claim his interests in a controversy with the client;
3) when a controversy arises concerning his power of representation; or
4) to perform his obligations as expressly provided otherwise by law.

12. *Conflict of Interests*

Any advocate may not enter into a contract to render professional service when he knows that there exists conflict of interests between the client and himself, or between his relatives and his client, or between his partners and his client, or between his clients. When the existence of conflict of interests has been discovered after the service had already begun the advocate shall explain the matter to his client and terminate the service.

13. *Conflict of Interests with Former Client*

1) Any advocate who has formerly rendered legal service in a matter or related other matters may not represent on the same matter a new client whose interests are adverse to the former client unless the former client consents, after consultation, in writing.
2) Any advocate may not represent a new client whose interests are adverse to a client to whom the firm, with which the advocate was formerly associated, had previously rendered legal service and about whom the advocate had acquired any information, unless the former client consents after consultation, in writing.

14. *Contracts Between Advocate and Client*

Any advocate may not enter into, with the client, any contract unless the following conditions are fulfilled:

1) the contract between the advocate and the client is proper and reasonable in view of the time and the situations;
2) the advocate clearly explains to the client the terms of the agreement and type of the contract; or
3) the client consents in writing to the agreement after consultation with another person.

፲፭· ከደንበኛ ስለሚደረግ ስጦታና ኑዛዜ

ማንኛውም ጠበቃ ደንበኛው በመልካም ፈቃዱ የሚያደርግለትን ኑዛዜ ወይም ከፍተኛ ዋጋ ያለውን ስጦታ ሊቀበል የሚችለው ጉዳዩ በጽሑፍ ከሆነና ድርጊቱ በሚፈጸምበት ጊዜ ደንበኛው ተገቢው የምክር አገልግሎት የተሰጠውና ስለድርጊቱም ውጤት ከገለልተኛ ጠበቃ የተረዳ መሆኑን ካረጋገጠ ብቻ ነው።

፲፮· በጠበቃና በደንበኛ መካከል ስለሚደረግ ብድር

ማንኛውም ጠበቃ ከደንበኛው ገንዘብ ሊበደር ወይም ለደንበኛው ገንዘብ ሊያበድር አይችልም።

፲፯· ጠበቃ ሽሪክ በሆነበት የንግድ ድርጅት ስለሚሰጠው የምክር አገልግሎት

ማንኛውም ጠበቃ ሽሪክ በሆነበት የንግድ ድርጅት ውስጥ አጠቃላይ የንግድ ድርጅቱን ወይም ሦስተኛ ወገኖችን በተመለከተ የምክር አገልግሎት ለመስጠት ይችላል፤ ሆኖም ራሱን በሚመለከት የድርጅቱ ጉዳይ ላይ የምክር አገልግሎት ለመስጠት አይችልም።

፲፰· የመንግሥት ሠራተኛ የነበረ ጠበቃ

፩· ማንኛውም ከዚህ ቀደም የመንግሥት ሠራተኛ ወይም ባለሥልጣን የነበረ ጠበቃ በቀጥታ በወሰነባቸው ወይም በጥልቀት በተሳተፈባቸው ጉዳዮች ላይ ከቀድሞ አሠሪው ጋር ተመካክሮ የጽሑፍ ፈቃድ ካልተሰጠው በስተቀር ለአንድ ደንበኛ የሙያ አገልግሎት መስጠት አይችልም።

፪· ሕግ በግልጽ ካልፈቀደ በስተቀር የመንግሥት ሠራተኛ ወይም ባለሥልጣን በነበረበት ጊዜ አንድን ግለሰብ በተመለከተ መረጃ ያገኘ ጠበቃ መረጃው ከሚመለከተው ሰው ጥቅም ጋር የሚጻረር ጥቅም ላለው ሰው የጥብቅና አገልግሎት ሊሰጥ አይችልም።

፲፱· ዳኛ ወይም የሽምግልና ዳኛ ወይም አስታራቂ

፩· ማንኛውም ጠበቃ ቀደም ሲል በዳኝነት ወይም አንድን ወገን በመወከል ሳይሆን በገለልተኝነት በሽምግልና ዳኝነት የተካፈለበትን ወይም በአስታራቂነት ወይም በሕግ ጉዳይ ፀሐፊነት የተሳተፈበትን ጉዳይ በሚመለከት በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን የጥብቅና አገልግሎት ሊሰጥ አይችልም።

፪· ማንኛውም ጠበቃ በዳኝነት ፡ በሽምግልና ዳኝነት ፡ በአስታራቂነት፥ በሕግ ጉዳይ ፀሐፊነት ወይም በተመሳሳይ ኃላፊነት በሚሠራበት ወቅት በዚሁ ጉዳይ ተካፋይ የሆነ ባለጉዳይ ወይም የሕግ ባለሙያ በሠራተኛነት እንዲቀጥረው ሊደራደር አይችልም።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተከለከለ ጠበቃ አባል የሆነበት የጥብቅና አገልግሎት ድርጅት ጠበቃው አገልግሎት እንዳይሰጥ በተከለከለበት ጉዳይ ላይ በሌላ ጠበቃ አማካኝነት አገልግሎት ሊሰጥ የሚችለው፤

ሀ) የተከለከለው ጠበቃ በጉዳዩ ላይ ምንም ዓይነት ተሳትፎና ከአገልግሎት ክፍያውም ድርሻ እንዳይኖረው ከተደረገ፥

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ለተመለከተው ጉዳዩን ላየው አካል ይህ ደንብ አለመጣሱን እንዲያረጋግጥ ይደረግ ዘንድ ተገቢው የጽሑፍ ማስታወሻ በወቅቱ የተላከለት ከሆነ።

፳· የአስታራቂነት ሥራ መሥራት

፩· ማንኛውም ጠበቃ ከዚህ የሚከተሉትን ድንጋጌዎች በመከተል በሁለት ደንበኞች መካከል በአስታራቂነት ሊሠራ ይችላል፥

15. *Gifts and Wills by Client*

Any advocate may accept a gift of considerable value or a will made to him by his client's free will only when the matter is in writing, and the advocate ascertains that the client had been represented by an independent advocate and given the proper advice concerning the consequences of his act.

16. *Loans Between Advocate and Client*

Any advocate may not lend money to, or borrow money from his client.

17. *Consultancy Service of an Advocate with Partnership in a Business Organization*

Any advocate who is a partner in a business organization may render advice regarding the business organization in general or third parties; he may not, however, render advice in the matter of the organization regarding himself.

18. *Advocate who Formerly was a Civil Servant*

1) Any advocate who formerly was a public employee or officer may not render professional service to a client in matters on which he passed decisions directly or participated in substantially unless he obtains the written consent of the former employer after consultation.
2) Unless otherwise provided by law, an advocate who has acquired information about a person while he was a public employee or officer may not represent a client whose interests are adverse to that person of whom the information is about.

19. *Former Judge or Arbitrator or Conciliator*

1) In no case may any advocate render advocacy service in a matter in which he had participated as a judge or arbitrator or conciliator.
2) Any advocate may not negotiate for employment with any person who was a party or a lawyer in a matter in which he had served as a judge, arbitrator, conciliator, legal clerk or similar other position.
3) A legal firm in which an advocate disqualified by sub-article (1) of this article is a member may continue representation, through another advocate, in a matter in which the member advocate is prohibited if:
   (a) the disqualified advocate is screened from any participation in the matter and is apportioned no part of the fee therefrom;
   (b) Written notice is promptly given to the appropriate body which handled the case as indicated by sub-article (1) of this article to enable it ascertain compliance with the provisions of these regulations.

20. *Working as Conciliator*

1) Any advocate may act as a conciliator between clients in accordance with the following provisions, if:

ሀ) ጠበቃው ሁለት ደንበኞችን ለማስታረቅ መሥራቱ፥ የሚኖረውን አንድምታ፥ ጥቅምና ጉዳቱን ጨምሮ ካስረዳቸው በኋላ ሁለቱም ደንበኞች በጠበቃው አስታራቂነት የተስማሙ ሲሆን፥

ለ) በጠበቃው ሚዛናዊ ግምት ጉዳዩ ከሁለቱ ወገኖች ጥቅም ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ይፈታል ብሎ ሲያምን፥ በተለይም እያንዳንዱ ደንበኛ በጉዳዩ ላይ አጥጋቢ ውሣኔ ለመስጠት ይችላል ብሎ ሲገምት፥

ሐ) ጉዳዩ በእርቅ ሳይፈታ ቢቀር በየትኛውም ወገን ጥቅም ላይ መሠረታዊ የሆነ ጉዳት ይደርሳል ተብሎ የማይጠበቅ ሲሆን፥ እና

መ) ሁለቱን ደንበኞቹን በጋራ የመወከሉን ኃላፊነት በገለልተኝነት ለመወጣት የሚችልና የትኛውም ወገን ላይ ተገቢ ያልሆነ ተጽዕኖ የማያሳድር መሆኑን ሲያረጋግጥ።

፪. ማንኛውም ጠበቃ የአስታራቂነት አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ ከእያንዳንዱ ደንበኛ ጋር የሚደረስበትን ውሣኔ በመመካከር እና በጉዳዩ ላይ ውሣኔ ለመስጠት የሚረዱትን ቁም ነገሮች በሙሉ እንዲገነዘቡ በማድረግ እያንዳንዱ ደንበኛ የተሟላና አጥጋቢ ውሳኔ እንዲሰጥ መርዳት አለበት።

፫. ማንኛውም ጠበቃ ከደንበኞቹ አንዱ የአስታራቂነት አገልግሎቱን እንዲያቋርጥ በጠየቀ ጊዜ ወይም በንዑስ አንቀጽ (፩) ከተመለከቱት ሁኔታዎች አንዱን መሟላት ባልቻለ ጊዜ የአስታራቂነት አገልግሎቱን ያቋርጣል። ውክልናውን ከአቋረጠም በኋላ በዚያው ጉዳይ ላይ ለማንኛውም ወገን የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት አይችልም።

**፳፩. ለድርጅት ጠበቃ ስለመሆን**

፩. ለአንድ ድርጅት የጠበቃ አገልግሎት የሚሰጠው በድርጅቱ ደንብ መሠረት አግባብ ያላቸውን የድርጅቱን የሥራ ኃላፊዎች እያማከረ ይሆናል።

፪. ማንኛውም ጠበቃ የድርጅቱ ተወካይ ሆኖ በሚሠራበት ወቅት የድርጅቱ ባለሥልጣን ፡ ተቀጣሪ ወይም ከድርጅቱ ጋር ተባባሪ ሆኖም የሚሠራ ሌላ ሰው ድርጅቱን በሕገ ወጥነት ሊያስጠይቅ በሚችል ሁኔታ አንድን ድርጊት በመፈፀም ወይም ባለመፈጸም በድርጅቱ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል ብሎ በገመተ ጊዜ ጉዳቱን ለመከላከል ይቻል ዘንድ አስፈላጊውን ሕጋዊ እርምጃ መውሰድ አለበት። በጠበቃው ሊወሰዱ ከሚችሉ እርምጃዎች የሚከተሉት ይገኙበታል።

ሀ) ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ መጠየቅ፥

ለ) በጉዳዩ ላይ የተለየ አስተያየት ቀርቦበት ሥልጣን ላለው የድርጅቱ አካል እንዲቀርብ ምክር መስጠት ፡ ወይም

ሐ) ጉዳዩን ከፍ ላለው የድርጅቱ አካል ማቅረብ ወይም ጉዳዩ አሳሳቢና ከባድ በሆነ ጊዜ ደግሞ ለድርጅቱ የመጨረሻ ውሳኔ ሰጭ አካል ማቅረብ።

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተመለከተው መሠረት ተገቢው ውሣኔ እንዲሰጥበት አስፈላጊው ጥረት ተደርጎ የመጨረሻ ውሳኔ ሰጭው አካል ሕግን የሚጥሰውና በድርጅቱ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትል የሚችለው እርምጃ እንዲቀጥል ከወሰነ ጠበቃው አገልግሎቱን በፈቃዱ መልቀቅ ይጠበቅበታል።

(a) the advocate explains the implications of the common representation, including the advantages and disadvantages involved, and both clients consent to the conciliation;

(b) the advocate reasonably believes that the matter can be resolved on terms compatible with the clients' best interests, especially that each client will be able to make adequate decisions in the matter;

(c) there is no substantial harm likely to happen to the interests of any of the clients if the contemplated resolution is unsuccessful; and

(d) the advocate ensures that the common representation can be undertaken impartially and without improper effect on either party.

2) while acting as a conciliator, any advocate shall consult with each client concerning the decisions to be made and explain the considerations relevant in making them, to help each client make complete and adequate decisions.

3) An advocate shall withdraw as a conciliator when any of the clients so requests, or if any of the conditions under sub-article(1) is not satisfied. He may, after withdrawal, not represent any of the parties on the matter.

21. *Advocate to an Organization*

1) An advocate representing an organization renders service acting through the duly authorized individuals in accordance with the rules of the organization.

2) If an advocate on the course of representing an organization believes that an officer, employee of the organization or other person associated with the organization is engaged in an action or refuses to act in a manner that would be imputed to the organization as unlawful, and is likely to result in substantial injury to the organization, the advocate shall take the necessary legal measures to prevent the damage. The measures to be taken by the advocate may include the following.

(a) asking reconsideration of the matter;

(b) advising that a separate opinion on the matter be given for presentation to the appropriate authority in the organization; or

(c) referring the matter to higher authority in the organization or if the matter is serious, referral to the highest decision making authority in the organization.

3) If, despite the efforts in accordance with sub-article (2) of this article, the highest authority insists upon the act that is in violation of the law and is likely to result in substantial injury to the organization to continue, the advocate is expected to resign from his service.

፬· ጠበቃው የድርጅቱን መሪ፣ ባለሥልጣን፣ ሠራተኛ ፣ ባለአክሲዮን ወይም በድርጅቱ የታቀፈ ሰው ጉዳይ በሚያይበት ጊዜ የእነዚህ ሰዎች ጥቅም ከድርጅቱ ጥቅም ጋር የሚጋጭ መሆኑ ከታወቀ የሰውዬውን ማንነት ማስረዳት አለበት።

፭· የጥቅም ግጭትን በተመለከተ የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ አንድን ድርጅት ወክሎ የሚሠራ ጠበቃ የድርጅቱን መሪዎች፣ ባለሥልጣኖች፣ ሠራተኞች ፣ ባለአክሲዮኖች ወይም ሌሎች ሰዎችን በመወከል ሊሰራ ይችላል።

## ፳፪· ችሎታ ለሌለው ሰው ጠበቃ ስለመሆን

፩· ደንበኛው ለአካለ መጠን ባለመድረሱ፣ የአእምሮ መታወክ የገጠመው በመሆኑ ወይም በሌላ በማናቸውም ምክንያት ከውክልናው ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ተገቢውን ውሳኔ ለመስጠት ባልቻለ ጊዜ ጠበቃው የጠበቃና የደንበኛን መደበኛ ግንኙነት በመጠበቅ መሥራት አለበት።

፪· ጠበቃው ደንበኛው የራሱን ጥቅም በአግባቡ ለማስ ጠበቅ የማይችል መሆኑን በተረዳ ጊዜ ሞግዚት እንዲመ ደብለት ማድረግ ወይም ጥቅሙን ለማስጠበቅ የሚረዱ ሌሎች እርምጃዎችን መውሰድ ይኖርበታል።

## ፳፫· የሕግ ሙያ ያልሆኑ ተደራቢ ሥራዎች

፩· ማንኛውም ጠበቃ በሕግ ሙያ አገልግሎት በተሰማ ራበት ወቅት ተደራቢ የንግድ ወይም ሌላ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ሥራ የሚያከናውን በሆነ ጊዜ በተደራቢነት የሚሠራው ሥራ የሙያውን ታማኝነት፣ ነፃነት፣ ብቃትና ክብር እንዳይቀንሰው ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅበታል።

፪· ማንኛውም ጠበቃ ከሙያው ውጭ የሚያከናውነውን ተደራቢ ሥራውንና የተሳትፎውን መጠን ለደንበኛው የማስታወቅ ኃላፊነት አለበት።

፫· ማንኛውም ጠበቃ ከሙያው ውጭ የሆነ ተደራቢ ሥራ በሚሠራበት ወቅት ከደንበኞቹ ጋር የሚያደርገው ግንኙነት ከጥብቅና ሙያው ውጭ መሆኑን በግልጽ እንዲረዱለት ማድረግ ይጠበቅበታል።

፬· ማንኛውም ጠበቃ ከጥብቅና ሙያው ውጭ በሆነ ሥራ ተሰማርቶ የሚያገኘውን ገቢ በጥብቅና ሙያው ካገኘው ገቢ ለይቶ የሚያሳይ የሒሣብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ አለበት ።

## ፳፬· የደንበኛን ንብረት ስለመጠበቅ

፩· ማንኛውም ጠበቃ ከውክልናው ጋር በተያያዘ የደንበኛን ንብረት በአደራ በሚጠብቅበት ወይም በሚያስተዳድርበት ጊዜ በኢትዮጵያ ሕግ የታዘዙትን የጥንቃቄ እርምጃዎች በሙሉ የማክበር፣ አግባብነት ያለው ሕግ በሌለ ጊዜ ደግሞ ጠንቃቃ ባለንብረት የሚወስዳቸውን የጥንቃቄ እርምጃዎች የመውሰድ ግዴታ አለበት ።

፪· ማንኛውም ጠበቃ ደንበኛው በስሙ ንብረት የሚረከብ መሆኑን በግልፅ የሚያውቅ ካልሆነ በስተቀር የደንበ ኛውን ንብረት እንደተረከበ መረከቡን የማስታወቅ ግዴታ አለበት ።

፫· ማንኛውም ጠበቃ የደንበኛውን ንብረት በአደራ በሚጠ ብቅበት ወይም በሚያስተዳድርበት ወቅት ንብረቱን ለመተሳሰብና ለባለመብቱ ለማስረከብ በሚያመች ሁኔታ መዝግቦ የመያዝ ግዴታ አለበት ። በባንክ መቀመጥ ያለበት ገንዘብ ካለም ለብቻው የተለየ የባንክ ሂሳብ መክፈት አለበት ።

4) In dealing with the cases of the organization's director, officers, employee, member, shareholder or other person, an advocate shall explain the identity of such person when it is known that the interests of the person is adverse to those of the organization's.

5) Without prejudice to the provisions of these regulations regarding conflict of interests, an advocate representing an organization may also represent the directors, officers, employees, members, shareholders or other constituents of the organization.

## 22. *Advocate to a Person under a Disability*

1) When a client is not able to make adequate decisions on matters connected with the representation due to minority, mental disability or for any other reason the advocate shall act maintaining client-advocate relationship.

2) An advocate shall seek the appointment of a guardian or take other actions for the protection of the interests of the client when the advocate thinks that the client cannot adequately act in line with his own interests.

## 23. *Non-professional Subsidiary Activities*

1) When an advocate engages in subsidiary commercial or other social, economic, political activities while rendering professional legal service, he is required to take the necessary care so that such subsidiary activities may not affect the loyalty, independence, competence and honor of his advocacy profession.

2) Any advocate shall have the responsibility to notify to his client the subsidiary activities he performs outside his profession and the extent of his participation.

3) Any advocate is required to explain clearly to his clients that he is not acting in his professional capacity when he deals with them in his subsidiary non professional activities.

4) Any advocate shall keep books of account which shows separately the income he collects from activities outside his advocacy profession from that he collects from his professional legal service.

## 24. *Keeping Client's Property*

1) When an advocate keeps on trust or administers the property of a client in connection with a representation, he shall respect all the cautionary measures that are provided under the Ethiopian law; in the absence of an appropriate law, he shall have the obligation to take the measures of care that are taken by a good owner.

2) Upon receiving the property of the client any advocate shall have the obligation to notify the client with same unless the client knows clearly that the advocate is receiving the property on his behalf.

3) When any advocate keeps on trust or administers the property of his client he shall have the obligation to maintain a record in a manner that is suitable for accounting and delivery of the property to the owner.

፬· ጠበቃው የያዛቸውን ንብረትና መረጃዎች ለማየት ሥልጣን የሌላቸው ሰዎች እንዳይመረምሩት ተገቢውን ጥንቃቄ የማድረግ ኃላፊነት አለበት ።

፭· ማንኛውም ጠበቃ ደንበኛው ንብረቱን ለመረከብ በጠየቀ ጊዜ ወይም ንብረቱን ለባለመብቱ ማስረከብ ተገቢ በሆነ ጊዜ የማስረከብ ኃላፊነት አለበት።

፮· ጠበቃው የደንበኛው ንብረት ባለአደራና አስተዳዳሪ በሆነበት ጊዜ በሦስተኛ ወገኖች የተያዘን ንብረት የማስመለስ፣ የደንበኛውን የባለንብረትነት ማረጋገጫ መዛግብትና ሌሎች መረጃዎች የማየት መብት አለው።

፳፭· የደንበኛን ልዩ ፈቃድ ስለማግኘት

ጠበቃ ለደንበኛው በሕግ የተፈቀደለትን የይርጋና ሌሎች ተመሣሣይ መብቶችን በተቃውሞነት በክርክር ወቅት ላያቀርብ የሚችለው ሁኔታውን ለደንበኛው ካስረዳ በኋላ ደንበኛው በጽሑፍ ከፈቀደለት ብቻ ነው።

፳፮· ጉዳዩ በስምምነት እንዲያልቅ ስለመገፋፋት

ጠበቃው የደንበኛው ጉዳይ በፍርድ ቤት ቀርቦ ከሚወሰን ይልቅ በእርቅ ቢያልቅ ተገቢውን ውጤት የሚያስገኝ ሆኖ ባገኘው ጊዜ ጉዳዩ በእርቅ እንዲያልቅ ሊገፋፋ ይችላል።

፳፯· የተከላካይ ጠበቃ ኃላፊነት

፩· ማንኛውም ተከላካይ ጠበቃ በደንበኛው ላይ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሊያሰጥ የሚያበቃ በቂ ማስረጃ መቅረቡን ካላረጋገጠ በስተቀር ደንበኛው በጥፋተኝነት እንዳይቀጣ የመከራከር ግዴታ አለበት ።

፪· ማንኛውም ጠበቃ ደንበኛው በተከሰሰበት ወንጀል ሙሉ ለሙሉ ጥፋተኛ መሆኑን ማወቁ ወይም በማስረጃነት የሚያቀርባቸው ነገሮች የማያዋጡ መሆናቸውን ማወቁ ለደንበኛው ተገቢውን የክርክር አገልግሎት እንዳይሰጥ ተጽእኖ ሊያሳድር እንደሚችል በመግለጽ ደንበኛውን አስቀድሞ ማስጠንቀቅ ይጠበቅበታል።

፫· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ የወንጀል ተከሳሽ በቀረበበት ክስ ጥፋተኛ ከመባሉ በፊት እያንዳንዱን የጉዳዩን ነጥብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ጠበቃው የሚያደርገውን ማጣራትና ክርክር አይመለከትም።

፳፰· አከራካሪ ጉዳይ በሌለበት ክስና ክርክር ስለአለማቅረብ

ማንኛውም ጠበቃ ተከራካሪን ለማጉላላት ክስ ማቅረብና መከራከር በተለይም አከራካሪ የሆነ ጭብጥ በሌለበትና የክርክሩ ውጤት በተከራካሪ ወገኖች መብት ላይ ለውጥ የማያመጣ መሆኑ በግልጽ በሚታይበት ጉዳይ ክስ ማቅረብና መከራከር አይችልም ።

፳፱· ለተቃራኒ ወገን ቅን ስለመሆን

ማንኛውም ጠበቃ የሚከተሉትን ድርጊቶች መፈጸም የለበትም፡

፩· ተቃራኒ ወገን ማስረጃ እንዳያገኝ ማናቸውም እንቅፋት መፍጠር ወይም ሌሎች ሰዎች ይህን መሰል አድራጎት እንዲፈጽሙ መምከር ወይም መርዳት፡

፪· ማስረጃን ማሳሳት ወይም ሌሎች ሰዎች ይህን መሰል አድራጎት እንዲፈጽሙ መምከር ወይም መርዳት፡

፫· ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት የሌለው ወይም በማስረጃ ሊደገፍ የማይችል ነገር ማቅረብ፣ በምስክርነት ካልቀረበ በስተቀር በግሉ የሚያውቀውን የጭብጥ ፍሬ ነገሮች መሰንዘር፣ ወይም የጉዳዩን ፍትሃዊነት፣ የአንድን ምስክር ተአማኒነት፣ የተከሳሽን ጥፋተኛ ወይም ተጠያቂ መሆንና አለመሆን አስመልክቶ የግል አስተያየቱን መስጠት፡

፬· ደንበኛው ወይም ምስክርነታቸውን እንዲሰጡ የማይገደዱ ሰዎችን በተመለከተ ካልሆነ በስተቀር ሌላ ማንኛ ውንም ሰው ለተቃራኒ ወገን የምስክርነት ቃሉን ወይም ሌላ አግባብነት ያለው መረጃ እንዳይሰጥ መገፋፋት።

4) The advocate shall have the responsibility to take the necessary care so that the property and documents in his possession may not be inspected by persons having no authority.

5) Any advocate shall have the responsibility to deliver to the client the property in his possession when the client so requests or when it is the right time to do so.

6) When the advocate keeps and administers his client's property he has the right to reclaim properties under possession of third parties, inspect his client's records of ownership title and other documents.

25. *Obtaining Client's Special Consent*

An advocate may decline to raise, as an objection in a proceeding, period of limitation and similar other rights provided by the law to the client only when he explains the matter to the client and the client consents thereto in writing.

26. *Encouraging the Consideration of a Case by Settlement*

When an advocate finds that the desired result can be obtained if his client's case can be resolved by settlement rather than in court he may encourage the consideration of the case by settlement.

27. *Responsibilities of a Defense Advocate*

1) Any defense advocate shall have the obligation to defend his client unless he is certain that adequate evidence has been produced to establish the guilt of the client by the court which has the authority.

2) Any advocate is required to warn his client beforehand the fact that to the advocate's knowledge that the client is guilty or that the things to be produced as evidences are not reliable may affect the advocate in giving the proper defense service to the client.

3) The provisions of sub-article (2) of this article shall not affect the inquiry and defense to be made by an advocate to ascertain that every element of the case be established before an accused in a criminal proceeding is held responsible.

28. *Claims and Contentions without Cause of Action*

Any advocate may not bring a case and defend a proceeding to harass an opposing party, especially when it is clear that there is no issue in controversy and the result of the proceeding will not have any effect on the rights of both parties.

29. *Fairness to Opposing Party*

Any advocate shall not:

1) Create any obstruction on opposing party's access to evidence or assist or counsel others to do any such act;

2) Falsify evidence, counsel or assist others to do any such act;

3) Present a matter that is irrelevant to the case, or that will not be supported by evidence, assert personal knowledge of facts in issue exccept when testifying as a witness, or state a personal opinion as to the justness of the matter, the credibility of a witness, the guilt or liability of an accused;

4) Encourage any other person, except the client or persons not compelled by law to testify, to refrain from testifying or giving other relevant information to an opposing party.

፴· <u>በጠበቃ ያልወከለ ተከራካሪ ሲያጋጥም</u>

ማንኛውም ጠበቃ ጠበቃ ያልወከለ ተከራካሪ ባጋጠመው ጊዜ ጠበቃው ሆን ብሎ ይህንኑ ተከራካሪ ወገን ሊያሳስቱ የሚችሉ ድርጊቶች ከመፈጸም መቆጠብ አለበት ። ከተቻለም ጠበቃ ላልያዘው ተከራካሪ ጉዳዩን በተመለከተ የጠበቃ ሚና ምን እንደሆን ማስረዳት አለበት ።

፴፩· <u>የሦስተኛ ወገኖችን መብት ስለማክበር</u>

ማንኛውም ጠበቃ ለደንበኛው በሚሰጠው የጥብቅና አገል ግሎት ሦስተኛ ወገኖችን ማጉላላት ፣ ማዋረድ ወይም በእነዚሁ ወገኖች ላይ ተገቢ ያልሆነ ጫና መፍጠር፣ ሌላ መሠረታዊ ግብ በሌለው ወይም የሦስተኛ ወገኖችን ሕጋዊ መብት በሚጋፋ መንገድ ማስረጃ የማግኘት ዘዴ መጠቀም የለበትም።

፴፪· <u>ጉዳዩን በመገናኛ ብዙሃን ስለመግለጽ</u>

፩· ማንኛውም ጠበቃ በሕግ ሙያ አገልግሎቱ ምክንያት ያወቀውን መረጃ ለመገናኛ ብዙሃን ሊገልጽ የሚችለው በሚዛናዊ የህሊና ግምት የመረጃው መገለጽ የፍርድ ሂደትን የማያደናቅፍና የደንበኛውን ጥቅም የማይጎዳ ከሆነ ብቻ ነው።

፪· በንዑስ ቁጥር (፩) የተመለከተው ክልከላ ቢኖርም ዝርዝር ጉዳይ ውስጥ ሳይገባ ጠበቃው በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ለመገናኛ ብዙሃን መረጃ ለመስጠት ይችላል፣

ሀ) የክሱን ወይም የመከላከያውን ጠቅላላ ሁኔታ ወይም ዓይነት፣ እንዲሁም የወንጀል ጉዳይ ከሆነ የክሱን ዓይነት፣ በሕግ ካልተከለከለ በስተቀር የወንጀል ክሱን ወይም የመከላከያውን ዓይነት፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ሰዎች ማንነት፣

ለ) በሕዝብ መዝገብ ውስጥ የሰፈረን መረጃ፣

ሐ) በጉዳዩ ላይ የተሰጠውን ቀነ ቀጠሮ ወይም ጉዳዩ የደረሰበትን ደረጃ፣

መ) መረጃ ለመሰብሰብ የቀረበን የዕርዳታ ጥያቄና የተፈላጊውን መረጃ ዓይነት፣

ሠ) ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው በግለሰቦች ወይም በሕዝብ ላይ ከፍተኛ አደጋ ሊያስከትል ይችላል የሚል ግምት ካለ ስለዚሁ ሰው ባህርይ አደገኛነት ማስጠንቀቂያ።

፫· ጠበቃ በደንበኛው ላይ የተሰራጩትን አሉታዊ ዜናዎችና መግለጫዎች በማስተባበል የደንበኛውን ጥቅምና መልካም ስም ለማስጠበቅ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሚዛናዊ የሆነ የማስተባበያ ወይም የማለዘቢያ መግለጫ ለመገናኛ ብዙሃን ለመስጠት ይችላል።

፴፫· <u>የጥብቅና አገልግሎት ስለማቋረጥ</u>

፩· ማንኛውም ጠበቃ ለደንበኛው ሊሰጥ የገባውን የጥብቅና አገልግሎት ውል ለማቋረጥ የሚያስችል በቂና አሳማኝ ምክንያት ከሌለው በስተቀር በገባው የውል ግዴታ መሠረት የደንበኛውን ጉዳይ እስከ መጨረሻው የመከ ታተል ግዴታ አለበት ።

፪· ጠበቃው ለደንበኛው በገባው የውል ግዴታ መሠረት የደንበኛውን ጉዳይ እስከ መጨረሻው ለመከታተል ባልቻለ ጊዜ ሁኔታውን ለደንበኛው የመግለጽና አገልግ ሎቱን በማቋረጡ ምክንያት በደንበኛው ላይ ሊደርስ የሚችለውን ወጭና መጉላላት ለመቀነስ እንዲሁም ጉዳዩ በተቃና ሁኔታ በሌላ ጠበቃ ሊሸፈን የሚችልበትን ሁኔታ የማመቻቸት ግዴታ አለበት ።

30. *Dealing with Unrepresented Person*

When an advocate is dealing with an opposing party who is not represented by an advocate the opponent shall be told by the advocate what the role of the advocate is in the matter; hence, the advocate shall refrain from deliberate acts that would mislead his opponent.

31. *Respect for Rights of Third Parties*

In representing a client, an advocate may not use means that have no substantial purpose other than to delay, embarrass or burden third parties, or use methods of obtaining evidence that violate the legal rights of such persons.

32. *Publicity on Mass Media*

1) Any advocate may disclose information he obtained in the course of his legal service to the mass media unless it is reasonably believed that the disclosure of information would be prejudicial to the trial proceeding and the interest of the client.
2) Notwithstanding the restriction imposed by sub-article (1), an advocate may without elaboration provide information to the media on the following matters:
   (a) the general nature of the claim or defense; and in a criminal case, except where prohibited by law, the nature of the charged offense or the defense and the identity of the persons involved;
   (b) the information contained in a public record;
   (c) the scheduling or the stage of the matter in litigation;
   (d) a request for assistance in obtaining evidence and the type of evidence needed thereto;
   (e) a warning of danger concerning the behavior of a person involved, when there is reason to believe that there exists the likelihood ofsubstantial harm to an individual or to the public;
3) When it is found necessary to protect the interest and reputation of the client by countering disseminated prejudicial news and declarations about the client, the advocate may provide resonable discrediting or mitigating declarations to the media.

33. *Terminating Advocacy Service*

1) Unless there is sufficient and convincing reason to terminate the contract of advocacy service an advocate shall have the obligation to follow his clients case up to the end in accordance with his obligation in the contract.
2) When the advocate is not able, as the contract obliges him, to follow his client's case up to the end, he shall explain the matter to his client and shall have the obligation to make the necessary effort to minimize the cost and inconvenience that would be caused as a result of the termination and to get the matter be successfully covered by another advocate.

## ፴፬· አገልግሎት ለማቋረጥ በቂ ምክንያቶች

ጠበቃ ለደንበኛው የሚሰጠውን አገልግሎት ለማቋረጥ የሚያስገድዱ በቂ ምክንያቶች የሚከተሉትን ይጨምራል፡

፩· ይህን የሥነ ምግባር ደንብ ወይም ሌላ ሕግ የሚጥስ ከሆነ፡

፪· ጠበቃው የተወከለበት ጉዳይ በመታየት ላይ ባለበት ወቅት ደንበኛው በጉዳዩ አካሄድ ላይ አስነዋሪ እርምጃ የወሰደ ከሆነና ከጠበቃው የሚያገኘውን አገልግሎት ለወንጀል ወይም ለማታለል ድርጊት ከተጠቀመበት ፡ ወይም ክርክሩን በሌላ ሰው ላይ መጉላላትን ለማስከተል ወይም ጉዳት ለማድረስ የተጠቀመበት ከሆነ ፡

፫· ጠበቃው ጉዳዩን በአግባቡ ለመምራት ችሎታና ብቃት ያነሰው እንደሆነ ወይም ከጥብቅና ሥራው ከተወገደ ፡

፬· ደንበኛው ውክልናውን በተመለከተ ከጠበቃው የሚፈለግበትን ግዴታ ሳይወጣ ሲቀር እና ግዴታውን ካልፈጸመ አገልግሎት የሚያቋርጥ መሆኑን ጠበቃው ካስጠነቀቀው ፡

፭· በጠበቃውና በደንበኛው መካከል ሊኖር የሚገባው መተማመን አንዱ ወገን የማታለል ወይም የማጭበርበር ድርጊት በመፈጸሙ የተነሳ በከፍተኛ ሁኔታ የተናጋ ከሆነ ፡

፮· የጉዳዩን ሂደት በሚመለከት ጠበቃው ወሣኝ በሆኑ ነገሮች ላይ የሚሰጠውን የሕግ ምክር ደንበኛው ውድቅ በማድረጉ የተነሣ በሁለቱ ወገኖች መካከል ሊኖር የሚገባው መተማመን ከጠፋ ፡

፯· ደንበኛው ለጠበቃው መክፈል ያለበትን የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፍልና ሌሎችንም ወጭዎች እንዲተካ ተገቢው ማሳሰቢያ ተሰጥቶት ኃላፊነቱን ለመወጣት ፈቃደኛ አለመሆኑን በግልጽ ካሳየ ።

## ፴፭· አገልግሎት የሚያቋርጥ ጠበቃ ግዴታዎች

ማንኛውም ጠበቃ ውል ሲያቋርጥ የሚከተሉትን ግዴታዎች መወጣት አለበት ፡

፩· ለደንበኛው በቂ ማስታወቂያ መስጠት እና ደንበኛው ሌላ ጠበቃ እንዲወክል በቂ ጊዜ መስጠት ፡

፪· የደንበኛውን ንብረትና ሠነዶች ሥርዓት ባለው መንገድ ወዲያውኑ ማስረከብ ፡

፫· ስለጉዳዩ ደንበኛው የሚጠይቀውን ማንኛውንም መረጃ መስጠት ፡

፬· በደንበኛው እጅ የሚገኝ ማንኛውንም ሂሣብ መተሳሰብ፡ ወደፊት ለሚሠራ ሥራ የተቀበለውን ገንዘብ ከወጪ ቀሪውን ተመላሽ ማድረግ ፡

፭· ለሥራ ማስኬጃ የተረከባቸውን ሂሣቦች መተሳሰብና ከወጪ ቀሪ መመለስ ፡

፮· ከተተኪው ጠበቃ ጋር በመተባበር በጉዳዩ መጓተት ፡ መቋረጥ ወይም አላስፈላጊ ወጭ እንዳያጋጥመው መከላከል ።

## ፴፮· የተተኪ ጠበቃ ግዴታዎች

፩· ተተኪው ጠበቃ ደንበኛው ከቀድሞ ጠበቃው ጋር ያለውን ማንኛውንም ሂሣብ እንዲያወራርድ ማስገንዘብ ይጠበቅበታል ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ደንበኛው ለቀድሞ ጠበቃው መክፈል ያለበትን የአገልግሎት ክፍያ አለማጠናቀቁ አዲሱ ጠበቃ በቀጠሮ ቀን በፍርድ ቤት ተገኝቶ ተገቢውን አገልግሎት እንዳይሰጥ ሊያግደው አይችልም ።

## 34. *Sufficient Grounds for Termination*

Sufficient grounds to terminate representation include, among others, the following when;

1) the client's required advocacy service is in violation of these Regulations or other law;
2) while in the course of trial of the matter for which the advocate is represented the client commits an act which is repugnant to the proceeding, the client has used the advocate's service to perpetrate a crime or fraud or the client has used the proceeding to cause inconvenience or cause damage on other person;
3) the advocate lacks the competence and ability to properly manage the case or he is discharged from his profession;
4) the client fails to fulfill an obligation to the advocate regarding the representation and has been given notice by the advocate that will terminate the service unless the obligation is fulfilled;
5) the mutual trust that should have been present between the advocate and the client has been greatly damaged due to fraud or deceit committed on the part of either party;
6) the mutual trust that should have been present between th two parties has been weakened becuse the client denounces the advice given by his advocate on matters that are decisive to the case;
7) the client shows clearly that he is not willing to fulfill his obligation to pay fees and reimburse other expenses to the advocate, after he has been given the proper notice.

## 35. *Obligations of an Advocate on Termination*

Any advocate terminating contract of Advocacy service shall fulfill the following obligations:

1) Give reasonable notice to the client and reasonable time to allow the client represent other advocate;
2) Properly surrender the property and records of the client immediately;
3) Give any information the client requests regarding the case;
4) Audit any account found in the client's hands, return the money left from payment received for a future work;
5) Audit the accounts he received in advance for the management of the case and return the money left;
6) In cooperation with the replacing advocate, protect the case against delay, interruption or unnecessary expenses.

## 36. *Obligations of Replacing Advocate*

1) The replacing advocate is required to inform his client to audit any account the client has with the former advocate.
2) The provision of sub-article (1) of this article that the client has not completed the fee to be paid to the former advocate shall not prohibit the new advocate from rendering the proper service on the fixed date, in court.

፴፯· በሽሪክ ወይም በተቆጣጣሪ ጠበቃ ስለሚሰጥ የጥብቅና አገልግሎት

፩· የጥብቅና ድርጅት ሽሪክ የሆነ ጠበቃ በድርጅቱ ውስጥ የሚሠራ ማንኛውም የሕግ ባለሙያ ይህን የሥነ ምግባር ደንብ ማክበሩን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል ።

፪· ማንኛውም ሌላውን ጠበቃ በቀጥታ የመቆጣጠር ሥልጣን ያለው ጠበቃ በእርሱ ሥር የሚያገለግል ጠበቃ የሙያውን የሥነ ምግባር ደንብ ማክበሩን የመቆጣጠር ኃላፊነት አለበት ፤

፫· ማንኛውም ጠበቃ ለሌላ ጠበቃ የሥነ ምግባር ጉድለት ተጠያቂ የሚሆነው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው ፤

ሀ) ጥፋት የፈጸመው ሰው ድርጊቱን የፈጸመው በጠበቃው ትዕዛዝ ሲሆን ወይም ጉድለት እየተ ፈጸመ መሆኑን እያወቀ ድርጊቱን ያጸደቀው ሲሆን፡

ለ) ጥፋት የፈጸመው ሰው ጠበቃው በሚሠራበት የጥብቅና አገልግሎት ድርጅት ሽሪክ ከሆነ ወይም በጠበቃው ቀጥተኛ ቁጥጥር ሥር የሚሠራ ከሆነና ግለሰቡ በሥነ ምግባር ደንብ የሚያስቀጣ ድርጊት እየፈጸመ መሆኑን እያወቀ ድርጊቱ የሚያስከት ለውን የማስተካከያ እርምጃ ያልወሰደ ሲሆን ።

፴፰· ክልከላ

፩· በማንኛውም የጥብቅና አገልግሎት ድርጅት ውስጥ የሚሠራ ጠበቃ በድርጅቱ ውስጥ ከሚሠሩት ሌሎች ጠበቃዎች አንዱ በዚህ ደንብ መሠረት አንድን ጉዳይ በጥብቅና ለብቻው ከመያዝ የሚያግደው ምክንያት መኖሩን እያወቀ የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት አይችልም ።

፪· የሚከተሉት ሁኔታዎች ካላጋጠሙ በስተቀር የጥብቅና አገልግሎት ድርጅትን የለቀቀ ጠበቃ በድርጅቱ ውስጥ በነበረበት ጊዜ ወክሎት ከነበረ ደንበኛ ጥቅም ጋር የሚጋጭ ጥቅም ያለው ደንበኛን ድርጅቱ ከመወከል አያግደውም ።

ሀ) ጉዳዩ ከዚህ ቀደም ለድርጅቱ የቀረበ ወይም ከቀድሞው ጉዳይ ጋር መሠረታዊ በሆነ መንገድ የተያያዘ ከሆነ ፤

ለ) በጥብቅና አገልግሎት ሰጭ ድርጅቱ ውስጥ ያለ ጠበቃ በቀረበው ጉዳይ ላይ በማስረጃነት ሊያገ ለግል የሚችል መረጃ በእጁ የሚገኝ ከሆነ ፤

፫· በዚህ አንቀጽ የተጣለው ክልከላ ጉዳዩ የሚመለከተው ደንበኛ ክልከላው ተፈጻሚ እንዳይሆን በጽሑፍ በተስማማ ጊዜ ቀሪ ይሆናል ።

፴፱· የበታች ጠበቃ ግዴታ

፩· በሌላ ጠበቃ አመራር ሥር የሚሠራ ማንኛውም ጠበቃ ይህን የሥነ ምግባር ደንብ ማክበር አለበት ።

፪· የበታች ጠበቃ አከራካሪ በሆነ የሥነ ምግባር ጥያቄ ላይ የበላዩን ትዕዛዝ በመቀበል የሠራ መሆኑን ለማስረዳት በቻለ ጊዜ ከተጠያቂነት ነፃ ይሆናል ።

፵· የሕግ ሙያተኛ ያልሆኑ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን ስለመቆጣጠር

የሕግ ባለሙያ ያልሆነን ሰው በተቀጣሪነት ወይም ለሚሰጠው አገልግሎት የተወሰነ ክፍያ በመስጠት ወይም በተባባሪነት የሚያሠራ ጠበቃ ወይም ጥብቅና አገልግሎት ድርጅት ፤

፩· ተገቢውን የጥንቃቄ እርምጃና ተፈላጊውን ቁጥጥር በማድረግ የግለሰቡ ምግባር ይህን የሥነ ምግባር ደንብ እንዳይጥስ ይቆጣጠራል ፤

37. *Advocacy Service Rendered by a Partner or Supervisory Lawyer*

1) An advocate who is a partner in a law firm shall ensure that any other lawyer in the firm conforms to these Regulations.
2) Any advocate who has supervisory authority over another advocate shall have the responsibility to supervise that the other advocate conforms to these regulations.
3) An advocate shall be responsible for another advocate's violation of these Regulatins if:
   (a) The lawyer orders or, with knowledge of the conduct, ratifies it,
   (b) While the person at fault is a partner of the advocate or works under the direct supervison of the advocate, the advocate knows of the punishable conduct at a time when its consequences can be avoided or mitigated but fails to take reasonable remedial action.

38. *Disqualification*

1) Any advocate who is working in an advocacy firm may not render service when he knows that there is a reason, in accordance with these Regulations, that would prohibit any of the other advocates in the firm to handle the matter alone.
2) The firm is not prohibited from thereafter representing a person with interests adverse to those of a client represented by the formerly associate advocate unless the following conditions are present:
   (a) The matter has been presented to the firm before or is substantially related to the formerly dealt matter by the firm;
   (b) An advocate remaining in the firm has information in his hands that can be used as evidence on the matter.
3) The disqualification imposed by this article may be waived when the client involved in the matter consents to its application, in writing.

39. *Obligations of a Subordinate Advocate*

1) Any advocate who is acting at the order of another advocate shall respect these Regulations.
2) A subordinate advocate shall be free from being responsible when he proves that he acted in accordance with the direction of his superior on an arguable ethical questions.

40. *Supervision of Nonlawyer Assistants to Advocate*

An advocate or advocacy firm who employs, or retains, or associated with, a person who is a non lawyer shall:

1) supervise that the person's conduct is compatible with these Regulations by taking the appropriate measures and making the necessary supervision;

፪· የሕግ ሙያተኛ ያልሆነው ባልደረባ ለፈጸመው የሥነ ምግባር ጉድለት ጠበቃው ተጠያቂ የሚሆነው ፤
  ሀ) ድርጊቱን እንዲፈጽም ያዘዘው ከሆነ ወይም የተፈጸመውን ድርጊት የሚያውቅ ከሆነና አፈጻጸሙንም የፈቀደ ወይም ያጸደቀ ከሆነ ፤
  ለ) ሙያተኛ ባልሆነው ሰው ላይ የቁጥጥር ሥልጣን ኖሮት የሥነ ምግባር ጉድለት የሆነውን ድርጊት መፈጸሙን እያወቀና ድርጊቱ የሚያስከትለውን ውጤት ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ እየቻለ ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ያልወሰደ ከሆነ ፤

ነው ።

፵፩· ሙያዊ ነፃነት

፩· ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት በሚከተሉት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር የጥብቅና አገልግሎት ክፍያን ጠበቃ ካልሆነ ሰው ጋር መካፈል አይችልም፤
  ሀ) ጠበቃው ከጥብቅና ድርጅቱ፣ ከሸሪኩ ወይም ተባባሪው ጋር በሚያደርገው ስምምነት መሠረት በሚሞትበት ጊዜ ወደ ሟቹ ጠበቃ ሀብት ወይም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለይቶ ላስታወቃቸው ሰዎች የሚደረግ ክፍያ፣
  ለ) ከሟች፣ ችሎታ ካጣ ወይም ከጠፋ ጠበቃ ላይ የጥብቅና አገልግሎት ድርጅት የገዛ ሰው ለሟች ጠበቃ ሀብት ወይም ለተወካዩ የሚፈጽመው የግዥ ክፍያ፣
  ሐ) ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የሕግ ባለሙያ ላልሆኑ ሠራተኞች የአገልግሎት ወይም የጡረታ ዋስትና ተጠቃሚ ከሚያደርገው ስምምነት ውስጥ በመግባቱ የሚደረግ ክፍያ ።

፪· ማንኛውም ጠበቃ የሕግ ሙያተኛ ካልሆነ ሰው ጋር የጥብቅና አገልግሎትን የሚያካትት የሽርክና ግንኙነት መመሥረት ወይም ሙያዊ ግዴታውን በመወጣት ረገድ የሕግ ሙያተኛ ላልሆነ ሰው የመምራትና የመቆጣጠር ሥልጣን በሚሰጥ ሁኔታ መሥራት አይችልም።

፵፪· የአገልግሎት ክፍያ አተማመን

ማንኛውም ጠበቃ ከደንበኛው የሚጠይቀው የአገልግሎት ክፍያ ተገቢና ሚዛናዊ መሆን አለበት። የክፍያውን መጠን ለመወሰን የሚከተሉትን መመዘኛዎች ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፣

፩· ለደንበኛው የሚሰጠው አገልግሎት የሚወስደው ጊዜና የሚጠይቀው ድካም፣
፪· ጉዳዩን በሚገባ ለማከናወን የሚያስፈልገው ችሎታ፣ የጉዳዩ አዲስነት እና አስቸጋሪነት፣
፫· ከደንበኛው ጋር የሚደረገው የጥብቅና ሥራ ስምምነት የሌሎች ደንበኞችን ጉዳይ ተቀብሎ ለመሥራት የሚያስችል መሆን አለመሆኑን፣
፬· ተመሣሣይ ጉዳዮች በተለምዶ የሚያስከፍሉትን የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ መጠን፣
፭· ለክርክሩ መነሻ የሆነው የሀብት ግምት እና የሚገኘው ውጤት፣
፮· በጠበቃውና በደንበኛው መካከል ያለው የሙያ ግንኙነት ርዝመት፣ እና
፯· የጠበቃው የሥራ ልምድ ፣ ጥሩ ዝናና የሙያ ችሎታ፣ እና
፰· ሌሎች መሰል መመዘኛዎች።

2) be responsible for unethical conduct committed by the nonlawyer when:
  (a) The advocate orders the commission of the act or with the knowledge of the act, ratifies or allowş the act;
  (b) While having a supervisory authority over the nonlawyer and with the knowledge of the commission of the act, he fails to take the appropriate remedial action to avoid or mitigate the consequences of the act.

41. *Professional Independence*

1) An advocate or law firm may not share legal fees with a person who is not an advocate except:
  (a) An agreement by the advocate with the advocate's firm, partner or associate may provide for the payment of money, after the advocate's death, to the lawyers estate or to persons specified in the agreement as beneficiaries;
  (b) An advocate who purchases the legal firm of a deceased, disabled or disappeared advocate may pay to the estate or representative of that lawyer the agreed-upon purchase price;
  (c) A payment made because an advocate or legal firm has entered into an agreement that would make nonlawyer employees beneficiaries of compensation or retirement plan.

2) An advocate may not form a pratnership with a non-lawyer if any of th eactivities of the partnership consists of the practice of law or work under a condition where a non-lawyer directs or controls the activities of an advocate in carrying out his professional duties.

42. *Fixing Fees*

The fee any advocate requires from his client shall be fair and reasonable. The following factors must be considered in determining the amount of the fee:

1) the time and labour rquired of the service given to the client;
2) the skill required to perform the service properly, the novelty and difficulty of the case;
3) the likelihood that the particular agreement with a client will preclude the advocate from dealing with other clients' cases;
4) the fee customarily charged for similar legal services;
5) the amount the claim involved and the results obtained;
6) the length of the professinal relationship with the client;
7) the experience, reputation and ability of the advocate; and
8) similar other factors.

፵፫· የአገልግሎት ክፍያ ስምምነት

፩· የአገልግሎት ክፍያ ስምምነት በጽሑፍ የሚደረግና በተዋዋይ ወገኖች ወይም በወኪሎቻቸው የሚፈረም ሕጋዊ ሰነድ ነው።

፪· በጠበቃና በደንበኛ መካከል የሚፈፀም የአገልግሎት ክፍያ ስምምነት የሚከተሉትን መሠረታዊ ጉዳዮች ይወስናል፡

ሀ) ደንበኛው ለጠበቃው የሚከፍለውን አጠቃላይ ገንዘብ፣ ደመወዝ፣ የማካካሻ ክፍያ፣ የመጠባበቂያ ክፍያ ወይም ሌላ የክፍያ ሥርዓት በመግለጽ የአከፋፈሉን ስልትና ጊዜ፣

ለ) ጠበቃው በጉዳዩ ላይ የሚያስገኘውን የውጤት ዓይነት ወይም ዓይነቶች።

፵፬· መጠኑ ያልተወሰነ የአገልግሎት ክፍያ ስምምነት

የአገልግሎት ክፍያው ክርክሩ በሚያስገኘው የገንዘብ መጠን ላይ የተመሠረተ በሆነ ጊዜ ስምምነቱ የሚከተሉትን መሠረታዊ ጉዳዮች የያዘ ይሆናል፡

፩· ጉዳዩ በስምምነት፣ በይግባኝ ወይም በሌላ መንገድ ቢያልቅ ከእነዚህ ሁኔታዎች ባንዱ ደንበኛው ከሚያገኘው ገንዘብ ላይ ለጠበቃው በመቶኛ ስሌት ሊከፈለው የሚገባውን የገንዘብ መጠን፣

፪· ለጠበቃው የሚደርሰው ሂሳብ የዳኝነት ክፍያ እና ሌሎች ወጭዎች ከተቀናነሱ በኋላ የሚታሰብ ወይም ከአጠቃላዩ ገንዘብ የሚታሰብ መሆኑን ።

፵፭· መጠኑ ያልተወሰነ የአገልግሎት ክፍያ የማይጠየቅባቸው ጉዳዮች

ጠበቃ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ያልተወሰነ የአገልግሎት ክፍያ ስምምነት ሊያደርግ አይችልም፡

፩· በመደበኛ ፍርድ ቤት በባልና ሚስት ክርክር ፍቺን በማስገኘት ላይ ተመስርቶ ወይም በሚያስወስነው የቀለብ ወይም የልጆች ማሳደጊያ ገንዘብ ወይም በሚያስገኘው የንብረት መጠን፣

፪· በወንጀል በተከሰሰ ሰው ላይ ፍርድ ቤት በሚሰጠው ውሳኔና ቅጣት ላይ ተመርኩዞ።

፵፮· በደንበኞች መካከል የጥብቅና አገልግሎት ክፍያን በድርሻቸው ስለማከፋፈል

በአንድ ጉዳይ ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎችን ወክሎ የሚከራከር ጠበቃ በተቃራኒው ግልጽ የሆነ ስምምነት ከሌለ በስተቀር የአገልግሎት ክፍያውን ፍትሐዊ በሆነ መንገድ እያንዳንዱ ደንበኛ ድርሻውን እንዲከፍል ያደርጋል።

፵፯· የአገልግሎት ክፍያን ከሌላ ጠበቃ ጋር ስለመካፈል

ማንኛውም ጠበቃ የአገልግሎት ክፍያን የሙያ ሸሪኩ ካልሆነ ሌላ ጠበቃ ጋር ለመካፈል የሚችለው፡

፩· ሌላው ጠበቃ በጉዳዩ ላይ አገልግሎት እንዲሰጥ ደንበኛው ቀጥተኛ በሆነ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የፈቀደ ሲሆን፣ እና

፪· የገንዘብ አከፋፈሉ እያንዳንዱ ጠበቃ ከሠራው ሥራና ከተቀበለው ኃላፊነት ጋር ተመጣጣኝ ሲሆን ብቻ ፡ ነው።

፵፰· የሕግ አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች አባል ስለመሆን

ማንኛውም ጠበቃ የጥብቅና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች አባል ለመሆን ይችላል ። ጠበቃው አባል የሆነበት ድርጅት በሚሰጣቸው ውሳኔዎች ወይም በሚወስዳቸው እርምጃዎች ላይ መካፈል የማይችለው ፡

፩· በውሳኔው ተካፋይ መሆኑ ከደንበኛው ጥቅም ጋር የሚጋጭ ሲሆን ፡

፪· አገልግሎት የሚሰጠው ሰው ወይም ማህበረሰብ ከጠበቃው ወይም ከጠበቃው ደንበኛ ጋር የማይጣጣም ጥቅምና ፍላጎት ያላቸው ሲሆን ፡

43. *Fee Agreement*

1) An agreement of fee is a legal document to be made in writing and signed by the parties to the agreement or their representatives.

2) A fee agreement to be made between advocate and client determines the following basic matters:

(a) the total amount of money, salary, reimbursement, reserve payment or other mode of payment to be made by the client and the method and time of payment.

(b) the kind of result or results to be obtained from the case by the advocate.

44. *Contingent Fee Agreement*

When the fee is contingent on the amount of the money obtained from the litigation, the agreement shall be determined based on the following basic matters.

1) The percentage that shall be paid to the advocate in each individual event if the case is resolved by settlement, appeal or other means;

2) Whether the amount that has to accrue to the advocate is calculated after court fees and other expenses are deducted or from the gross amount.

45. *Cases of Prohibition of Contingent Fee*

An advocate may not enter into an agreement for contingent fee on the following matters:

1) In a family matter, contingent upon the securing of a divorce or upon the decision on the amount of alimony or support for the upkeep of the children, or property settlement, in a court of law;

2) A fee contingent up-on the decision and penalty given by the court in a criminal case.

46. *Divison of Fee Among Clients*

Unless there exists an express agreement to the contrary an advocate who represents more than one person in a case shall arragne for a just payment of the fee by each client, according to his share.

47. *Division of Fee Between Advocates*

Any advocate may share a fee with other advocate who is not a partner in profession only if;

1) The client consents directly or indirectly to the involvement of the other advocate in the matter; and

2) The division of the fee is in proportion to the services performed and responsibility assumed by each advocate.

48. *Membership in Legal Services Organization*

Any advocate may be a member in a legal service organization. The advocate may not participate in decisions or actions of the organization where he is a member if:

1) his participation in the decision or action would conflict with the interests of his client;

2) the person or community which receives service has interests that are not compatible with the interest of the advocate or his client.

፵፱· ነፃ የሕግ አገልግሎት ስለመስጠት

ማንኛውም ጠበቃ በነፃ ወይም በአነስተኛ ክፍያ በዓመት ቢያንስ የ፶ ሰዓት የሕግ አገልግሎት መስጠት አለበት ። አገልግሎት የሚሰጠውም ፤

፩· የመክፈል አቅም ለሌላቸው ሰዎች ፤

፪· ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች ፣ ለሲቪክ ድርጅቶች ፣ ለማህበረሰብ ተቋማት ፤

፫· ፍርድ ቤት የጥብቅና አገልግሎት እንዲያገኙ ለሚጠይቃቸው ሰዎች ፤

፬· ሕግን ፣ የሕግ ሙያንና የፍትሕ ሥርዓቱን ለማሻሻል ለሚሠሩ ኮሚቴዎችና ድርጅቶች

ነው።

፶· አገልግሎትን አስመልክቶ ስለሚሰጥ መግለጫ

ማንኛውም ጠበቃ ስለ እራሱ ወይም ስለሚሰጠው አገልግሎት ሀሰተኛ ወይም የሚያሳስት መግለጫ መስጠት የለበትም ። ከጠበቃ የሚሰጥ መግለጫ ሀሰተኛ ወይም የሚያሳስት ነው ሊባል የሚችለው ፤

፩· ፍሬ ነገር ወይም ሕግ ያልሆነውን እንደሆነ አድርጎ ላቀረበ ወይም አንድን ፍሬ ነገር በመደበቅ አንድን አባባል እውነት አስመስሎ ካቀረበ ፤

፪· ጠበቃ በክርክር ሊያስገኘው የሚችለውን ውጤት አጋኖ በማቅረብ ተገቢ ያልሆነ ተስፋ እንዲፈጠር ከገፋፋ ወይም ይህን የሥነ ምግባር ደንብ የሚጥስ ዘዴን በመጠቀም ለጉዳዩ ውጤት ለማስገኘት ቃል የገባ ሲሆን፤

፫· በተጨባጭ ማረጋገጥ የሚቻል ካልሆነ በስተቀር አንድ ጠበቃ የራሱን የጥብቅና አገልግሎት ከሌሎች ጠበቆች አገልግሎት ጋር በማነፃፀር የራሱን አጉልቶ የሚያሳይ መግለጫ ከሰጠ ፤

ነው ።

፶፩· ደንበኛን አስመልክቶ ስለሚሰጥ መግለጫ

ማንኛውም ጠበቃ የደንበኛውን ጉዳይ አስመልክቶ ለሦስተኛ ወገኖች በፍሬ ጉዳዩም ሆነ በሕግ ረገድ ሃሰተኛ የሆነ መረጃ መስጠት አይችልም።

፶፪· ማስታወቂያ ስለማስወጣት

፩· ማንኛውም ጠበቃ የሚሰጠውን የሕግ አገልግሎት በሚለጠፍ ማስታወቂያና በሌሎች መገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች ማስተዋወቅ ይችላል ። ማስታወቂያው አጭር፣ ግልጽና ትክክለኛ ሆኖ የጠበቃውን ስም ፣ አድራሻ ፣ የሚሰጠውን አገልግሎትና የሥራ ልምድ መግለጽ ይኖርበታል ።

፪· ማንኛውም ጠበቃ ማስታወቂያውን ለመገናኛ ብዙሃን ከመላኩ ከሠላሳ ቀናት በፊት ለጥብቅና ፈቃድ ሰጭው አካል አንድ ኮፒ እንዲደርሰው ማድረግ አለበት ።

፫· በዚህ አንቀጽ መሠረት ለሚዘጋጅ ማስታወቂያ ይዘት ተጠያቂ የሚሆን ቢያንስ የአንድ ጠበቃ ስም መጨመር አለበት ።

፶፫· የሙያ ዘርፍን ስለማስተዋወቅ

፩· ማንኛውም ጠበቃ በተወሰነ የሕግ ዘርፍ አገልግሎት የሚሰጥ ወይም የማይሰጥ መሆኑን ማስታወቅ ይችላል።

፪· ጠበቃ በተወሰነ የሕግ ዘርፍ ልዩ ዕውቀት ወይም ጠበብትነት አለኝ ብሎ ለማስታወቅ የሚችለው የልዩ ዕውቀት ወይም የጠበብትነት ማዕረግ ለመስጠት በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል የምስክር ወረቀት ሲሰጠውና ምስክርነቱ በጥብቅና ፈቃድ ሰጪው አካል ሲታወቅ ነው ።

49. *Rendering Free Legal Services (Pro Bono Publico Service)*

Any advocate shall render at least 50 hours of legal service, in a year, free of charge or upon minimum payment. The service shall be rendered to;

1) persons who can not afford to pay,
2) charity organizations, civic organizations, community institutions;
3) persons to whom court requests legal service;
4) committees and institutions that work for improving the law, the legal profession and the justice system.

50. *Communications Concerning Services*

Any advocate may not give false or misleading communication about himself or his services. A communication given by an advocate is false or misleading if it:

1) contains a material misrepresentation of fact or law, or omits a fact to make a statement considered true;
2) creates an unjustified expectation about the results the advocate can achieve by exaggerating the possible results or the advocate promises that he can achieve results by means that violate these Regultions;
3) compares the services he renders with other advocates' services unless the comparison can be factually substantiated.

51. *Truthfulness in Statement to Others*

Any advocate may not give a false statement of material fact or law to a third person concerning his client.

52. *Advertising*

1) Any advocate may advertise the legal services he renders through outdoor advertising or other mass media. The advertisement shall be brief, clear and correct and shall contain the name and address of the advocate and, the service he renders and work experience.
2) Any advocate shall give a copy of the advertisement to the body that issues advocacy license 30 days before the advertisement is sent to mass media.
3) An advertisement prepared pursuant to this article shall include the name of at least one advocate responsible for its content.

53. *Advertising Fields of Profession*

1) Any advocate may communicate the fact that he does or does not render service in a particular field of law.
2) An advocate may communicate that he is a specialist in a particular filed of law when he is certified by the organ authorized by law to do so and the certification is acknowledged by the body issuing advocacy license.

፶፬· በድርጅት ስም ስለመጠቀም

፩· ማንኛውም ጠበቃ የሚጠቀምበት የጥብቅና አገልግሎት ድርጅት ስያሜ ከመንግሥት ፣ ከሕዝብ ወይም ከበጎ አድራጎት ድርጅት ስም ጋር የሚመሳሰል እስካልሆነ ድረስ የጥብቅና አገልግሎቱን በተወሰነ ስም ፣ ፊደላት ወይም ሌላ የሙያ ስያሜ ማስተዋወቅ ይችላል ።

፪· ከአንድ ክልል በላይ ወይም በተለያየ የሥልጣን እርከን ደረጃዎች አገልግሎት የሚሰጥ የጥብቅና ድርጅት በሚሠራባቸው ሥፍራዎች እራሱን በአንድ ስም ማስተዋወቅ ይችላል ፤ በሚያወጣው ማስታወቂያ ግን የሚሠራበትን ክልልና በእያንዳንዱ ክልል እንዲሠራ የተፈቀደለትን የሥልጣን እርከን መግለጽ አለበት ።

፫· የጥብቅና ድርጅት አባል የነበረ ጠበቃ በመንግሥት ኃላፊነት ላይ ሲሆን የዚህን ሰው ስም በድርጅቱ መጠሪያነት መገልገል ወይም ከድርጅቱ አባላት አንዱ የነበረ መሆኑን መግለጽ የተከለከለ ነው ።

፶፭· የሙያ ባልደረባን ስለማክበር

፩· ማንኛውም ጠበቃ ከሌሎች የሙያ ባልደረቦቹ ጋር የሚኖረው ግንኙነት በቅን ልቦና፣ በመከባበርና በመግባባት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ማድረግ አለበት፤

፪· በፍትህ መድረክ የሙያ ባልደረባን መዝለፍ፣ ማንቋሸሽ ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ ክብሩን ለመቀነስ መሞከር የተከለከለ ነው፡

፫· ማንኛውም ጠበቃ ከደንበኛው ወይም ከሌላ ጠበቃ ጋር የሚያደርገውን ንግግር ለመቅረጽ የሚፈልግ መሆኑን አስቀድሞ ሳያሳውቅ መቅረጽ የለበትም፤

፬· ማንኛውም ጠበቃ ከሙያ ባልደረባው ለሚደርሱት የሥራ ግንኙነት ደብዳቤዎች ተገቢውን ምላሽ የመስጠትና ይህን ግንኙነት አስመልክቶ የተደረገውን ስምምነት የማክበር ግዴታ አለበት ።

፭· የተለየ ስምምነት ካልተደረገ በስተቀር አንድ ጠበቃ የተከራካሪው ወገን ጠበቃ ሳያውቀው ወይም እርሱ በሌለበት ከተከራካሪው ጋር መደራደር የለበትም ።

፶፮· በክርክር ወቅት የጠበቃ ግዴታዎች

ማንኛውም ጠበቃ በክርክር ወቅት የሚከተሉትን ድርጊቶች ከመፈጸም መቆጠብ አለበት ፡

፩· በምቀኝነት ወይም በክፉ ልቦና ተነሳስቶ ሌላውን ወገን የሚጎዳ ክስ ወይም ክርክር ማቅረብ ፤

፪· ደንበኛው የወራዳነት ወይም የማጭበርበር ድርጊት እንዲፈጽም ማበረታታት ወይም መፍቀድ ፤

፫· ዳኛን ወይም ሌላ የፍርድ ቤት ሠራተኛን በሕግ መሠረት ከማሳመን ውጭ ሌላ ተገቢ ያልሆነ ማንኛውም ዓይነት ዘዴ በመጠቀም ተጽዕኖ ለማሳደር መሞከር ወይም በሌላ ሰው እንዲሞከር ማድረግ ፤

፬· ሆን ብሎ ፍርድ ቤትን የሚያሳስት ወይም የተጋነነ ጽሑፎችና ንግግር ማድረግ ፤

፭· በምስክርነት ቃል ወይም የሠነድ ይዘት ላይ የሐሰት ድርጊት በመፈጸም ፍርድ ቤትን ለማሳሳት መሞከር ፤

፮· በግልጽ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ማስረጃ አግባብነት ያለው አስመስሎ ለፍርድ ቤት ማቅረብ ፤

፯· ለጉዳዩ በምስክርነት መቅረብ የሚገባው ሰው ፍርድ ቤት እንዳይቀርብ ማግባባል ወይም መምከር ፤

፰· አንድን ምስክር ተገቢ ባልሆነ መንገድ ማመናጨቅ፣ ማስጨነቅ ወይም ማስፈራራት ፤

54. *Using Firm Name*

1) Any advocate may publicize his legal service by a particular name, letters or other professional designation unless the name he uses is similar to the name of a government, public or charitable organization.
2) A law firm which renders services in more than one region or in different hierarchies of jurisdictions may publicize itself in a single name; however, the advertisement shall indicate the region where the firm practices and the jurisdictional hierarchy licensed to practice.
3) The name of an advocate who formerly was a member in a firm and now holding a public office, may not be used in the name of a law firm or it may not be expressed that he was a member of the firm.

55. *Respect for Colleagues*

1) Any advocate shall make sure that his relations with the other professional colleagues is based on good faith, respect and understanding.
2) It is prohibited to insult, be little or in any other way attack the reputation of a fellow advocate in the justice forum.
3) Any advocate may not record the dialogue he holds with his client or other advocate without notifying them of his intention to do so.
4) Any advocate shall reply to letters of correspondence from his colleague and respect the agreement he entered into on this matter.
5) Any advocate may not sit for settlement in the absence of the opposing party's advocate without the knowledge of the said advocate, unless otherwise agreed.

56. *Obligations of Advocate in Proceedings*

Any advocate shall refrain from the following acts, in a proceeding;

1) institute a case or forward a litigation motivated by envy or bad faith to injure the other party,
2) encourage or allow a client to commit a repugnant or fraudulent act,
3) attempt to influence a judge or other official by means not acceptable other than to convince according to the law or seek the act to be done by another person,
4) intentionally make papers and statements which are exaggerated, mislead the court; or,
5) intentionally mislead the court by falsifying the testimonies of witnesses or the contents of a document,
6) produce to court as though relevant an evidence which is clearly irrelevant to the matter,
7) counsel or induce a person who is required as a witness, not to appear before court,
8) nag, traumatize or threaten a witness in methods that are inappropriate.

፶፯. <u>አስነዋሪ ከሆኑ ሥነ ምግባሮች ስለመራቅ</u>

ማንኛውም ጠበቃ በሕይወቱ ውስጥ የሙያውን ክብር ሊያጎድፍ ከሚችል ማንኛውም ዓይነት አስነዋሪ ባህሪ የራቀ መሆን አለበት ።

፶፰. <u>የሥነ ምግባር ጉድለት መፈጸሙን ስለማሳወቅ</u>

ማንኛውም ጠበቃ ከዚህ በታች የተመለከቱት መፈጸማ ቸውን እንዳወቀ ድርጊቱን የፈጸመውን ሰው ስምና የጥፋቱን ዓይነት በመግለጽ ለፈቃድ ሰጪው አካል ወይም በአካ ባቢው ለሚገኘው የፍትሕ አስተዳደር ባለሥልጣን የማስ ታወቅ ግዴታ አለበት ፡

፩. አንድ ጠበቃ ይህን ደንብ ጥሶ ከተገኘ ፤

፪. አንድ ሰው የጥብቅና ፈቃድ ሳይኖረው የጥብቅና አገልግሎት ሲሰጥ ከተገኘ፤ ወይም

፫. አንድ ጠበቃ በጥብቅና ፈቃዱ ከተፈቀደለት ውጭ ሲሠራ ከተገኘ።

፶፱. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ መስከረም ፲፫ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

57. *Refraining from Repugnant Acts*

Any advocate shall, in his life, refrain from any repugnant behavior which would harm the honor or his profession.

58. *Notifying Unethical Conduct*

Any advocate on knowledge of the following violation shall have the obligation to notify to the body issuing advocacy license or to the local justice administration authority or to the name of the advocate and the type of the violation.

1) where an advocate violates these regulations;
2) where a person renders legal service without having advocacy license;
3) where an advocate is found rendering advocacy service in violation of the conditions attached to the license.

59. *Effective Date*

These Regulations shall enter into force on the date of their publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa this 24th day of September, 1999.

MELES ZENAWI
PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA